# ጅንን ያልኩ አማራ

ሲደላኝ ኢትዮጵያ ፣ ሳዝን ምናምንቴ
በስሌት አይሰራም ፣ ኢትዮጵያዊነቴ
ጊዜ አይለውጠውም ፣ የኔን ማንነቴ
በክፉም በደጉም ፣ ኢትዮጵያ ናት ቤቴ ።

ምክን ያት ፈጥሬ ፣ ውንጀላ ደርድሬ
በባዕዳን ሴራ ፣ በዶላር ሰክሬ
ባገሬ አልዶልትም ፣ እኔም እንዳጅሬ
ፊቴን አላዞርም ፣ ጭራሽ በሀገሬ ።

አላለቃቅስም ፣ አልደላኝም ብዬ
ሰው አላስፈራራ ፣ ግንጠላን አዝዬ
ካልኖርኩኝ አልልም ፣ ሁሌ ተባብዬ
ፍቅሬ ልባዊ እንጂ ፣ አይደል ተደልዬ ።

ዘመን ሳይቆጠር ፣ ከሁሉ አስቀድሜ
በናት ሀገሬ ላይ ፣ የጠገብኩኝ እድሜ
ውስጤ ሲመረመር ፣ አጥንቴና ደሜ
መች አማራ ብቻ ፣ ኢትዮጵያም ናት ስሜ ።

በውልደት ቢመጣም ፣ ከናትና አባቴ
በመላው ኢትዮጵያ ፣ ተቀብሯል እትብቴ
ኢትዮጵያዊነት ነው ፣ ለኔ ዜግነቴ
ይሄንን አንግቤ ፣ ስታገል ለመብቴ
እሰባሰባለሁ ፣ በአማራዊነቴ
ግና ድሬም ማጌም ፣ ኢትዮጵያዊነቴ
ሁሌ እማላወልቃት ፣ ማተቤ ያንገቴ ።

አዎን አማራ ነኝ ፣ የሸዋ የወሎ
የማልቆረጠም ፣ የብረት አሎሎ
አማራ ነኝ እኔ ፣ የጎጃም የጎደር
በማንነቴ ላይ ፣ የማልደራደር
አዎን አማራ ነኝ ፣ ጅንንና ኩሩ
ደሜን ያፈሰስኩኝ ፣ በየዳር ድንበሩ
አማራ ነኝ ሁሌም ፣ አጥንት የማልቆጥር
በቋንቋ ሃይማኖት ፣ ከልዩ እማላጥር
ባለ ሙሉ ዝናር ፣ ጎፈሬ እማበጥር
ሲነኩኝ የማልወድ ፣ ቁጡ እንዳራስ ነብር ።

አማራ ነኝ እኔ ፣ ፍጹም ኢትዮጵያዊ
ጎጠኛን የማልወድ ፣ ወስላታና ሃሳዊ
አዎን አማራ ነኝ ፣ ቆፍጣና ነፍጠኛ
ለባንዳ ለበታኝ ፣ የቀትር መጋኛ
ልኩን ሳላሳየው ፣ እንቅልፍ የማልተኛ ።

እኮ ነኝ አማራ ፣ የቴዎድሮስ የበላይ
ተኩሼ የማልስት ፣ ወፍ አውራጅ ከሰማይ
ከጠላት አልራራ ፣ በቁም ሸንቶ ሳላይ
ሃሞተ መራራ ፣ ሁልግዜም አማራ
ብታገስ ከጀለው ፣ መስሎት የምፈራ
ሲነኩኝ አልወድም ፣ ከነኩኝ አልራራ
ብርክ ያዘው ተገንጣይ ፣ አማራው ሲጣራ
ስነሳ የማርድ ፣ እንኳንስ ተኩሼ
ወንዱን የምሸኘው ፣ ቀሚስ አስለብሼ ።

በኢትዮጵያዊነት ፣ ባገሬ የምኮራ
እንደ ምናምንቴ ፣ ዘር ጎሳ እማልጠራ
ከጠላት አላድር ፣ ሹምባሽ ሆኜ አልሰራ
ደንዳና ልብ ያለኝ ፣ ጅንን ኩሩ አማራ ።

ዝናሩን ታጠቀ ፣ አማራው ከተተ
ጎጠኛ ተንጫጫ ፣ ጬኸት በረከተ
ሱሪው እረጠበ ፣ በቁሙ እየሞተ
ጥይት እንኳን ሳይጮህ ፣ አለ እንደባተተ ።

በታኝ ተገንጣዩ ፣ ጠባብ የጠበበ
አማራው ተነሳ ፣ ብሎ ስላሰበ
ግብአተ መሬቱ ፣ ሞት ስለቀረበ
ያገር ሃብት ይዘርፋል ፣ እየሰበሰበ ።

የምዬ ሚኒሊክ ፣ ያፄ ኃይለስላሴ
አዎን አማራ ነኝ ፣ አላፍርም በራሴ
እና ምን ይጠበስ ፣ በኔነቴ ኮራሁ
እንደ ስም አይጠሬ ፣ አልሰረቅሁ አልቀማሁ
ትምክህተኛም ልባል ፣ ባንዳን ስለጠላሁ
ኮራ ብዬ እምሄድ ፣ አገሬን ያቀናሁ ።

አበጀሁ ልመካ ፣ ልሁን ትምክህተኛ
ጠብቤ አልተገኘሁ ፣ አይደለሁ ጎጠኛ
የሰራ ይመካል ፣ ያልሰራ ይፈርበት
ጀግና የጀግና ልጅ ፣ አይደለሁም እበት
ቀና ብሎ ይሄዳል ፣ በራሱ የሚመካ
ታሪክ ብልሹ ፣ ሁሌም ነገር ያቡካ
ለጣሊያን ያደሩ ፣ እያደገደጉ
ትምክተኛ ቢሉኝ ፣ አልቀር ብሎ ወጉ
ስለማይገባቸው ፣ ክብርና ማዕረጉ
ትምክህቴን ወደድኩት ፣ ዘሬ ነው ሃረጉ
ጅንን ያልኩ አማራ ፣ የበላይ የጅጉ
አዎን እመካለሁ ፣ እስቲ ምን ታደረጉ ።

ታዛቢው

June 10, 2018